ትምህርታዊ ሰነዶች

የህ የድህረ ገጽ ክፍል ስለ የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት እርሶን ሊጠቅም የሚችል ወይም ሌላ ሰው ሊረዱበት የሚችል መረጃ ያቀርባል።

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ምን እንደሆነ የበለጠ ያውቃሉ - የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ምን ዓይነት ድርጊቶችን እንደሚያካትት፤ የኢሚግሬሽን ጉዳይ እርስዎን እንዴት እንደሚነካና ስለ ሰው ልጆች ሕገ ወጥ ዝውውር ይረዳሉ ፡

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ምንድነው?

በሰውነትዎ ላይ፣ በወሲብ ግንኙነት፤ እና በስሜቶ ላይ በሚያውቁት ሰው እየተጎዱ ከሆነ፤ ያ የሚአውቁትም ሰው የቤተሰብዎ አባል ከሆነ፤ የልጅዎ አባት ወይም ከዚህ በፊት የፍቅር ጓደኛዎ በሆነ ሰው ከሆነ ይህ የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ነው።

ከሚጎዳዎ ሰው የመከልከል/የመራቅ መብት አሎት።

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት የሚፈፀመው አጥቂው ተጠቂውን በቁጣ፤በማስፈራራት፤ በወሲባዊ ግንኙነት ጉዳት፤ በመከታተል፤ በገንዘብ እና በመሳሰሉ ድርጊቶች በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ሲሞክር ነው።

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት አደገኛ፡ ነው እርምጃ ካልወሰዱበት እየባሰ ይሄዳል።

ከዚህ በታች የጉዳ ድርጊቶች ምሳሌዎች ዝርዝር ቀርበዋል ዝርዝሩ በፍቅር ጓደኛ ጥቃት እንዴት እየጨመረ እንደሚሄድና የአደገኝነቱን ከፍተኛ ደረጃ ያሳያል።

## ቀጣይ ግጭት/ሁከት/አደጋ

| ስሜታዊ ጉዳት | የወሲብ ጉዳት |
|---|---|
| • እየደጋገሙ መጮህና መሰደብ<br>• ስለ ኢሚግሬሽን ጉዳይ ውሸት ሲነገርዎ<br>• ለቤተሰብዎ ስለ እርስዎ ውሸት ሲነገር<br>• ባህልዎን ትተው አሜሪካዊ ሆነዋል ሲባሉ<br>• ስሜትዎ ሳይከበርና ሲንቋሸሽ<br>• የስሜት ድጋፍ እንደ ቅጣት ሲነፈጉ<br>• በግልና በሕዝብ መሀል ሲዋረዱ<br>• ወቀሳ ሲወቀሱ<br>• ትኩረትዎ አጥቂው ሰው ላይ ብቻ እንዲሆን ሲጠየቁ<br>• ትዳርዎ ላይና ልጆችዎ ላይ የማስፈራራት ዘመቻ ሲካሄድ<br>• በቂ አፍቃሪ ወይም የትዳር ጓደኛ አይደሉም ሲባሉ | • የወሲብ ቀልድ ወይም ያታዎን የሚያንቋሽሽ ንግግር መናገር<br>• ቅናት (ከሌሎች ጋር የወሲብ ግንኙነት አልዎት ብሎ መገመት<br>• የማይፈልጉት ዓይነት ንኪኪ መንካት<br>• የወሲብ ግንኙነቶትን መንቀፍ<br>• ወሲባዊ ተግባርን በመግለጽ መሳደብ<br>• የወሲብ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ፊልሞችን እነዲየዩ ማስገደድ<br>• የሚጎዳ የወሲብ ግንኙነት በወለዱ ወይም ቀዶጥገና ባደረጉ ሰዓት መጠየቅ<br>• አስገድዶ መድፈር<br>• ወሲባዊ ግንኙነትን እና ፍቅርን መንፈግ |

| | |
|---|---|
| • የፆታ ሚና አባባል እርሶን ለመጉዳት ሲተረክ<br>• ባህልዎ ወይም ሀይማኖትዎ ሲንቋሸሽ<br>• በህይወትዎ ላይ ሃላፊነት የሎትም ሲባሉ<br>• ዕብድ ኖት ሲባሉ<br><br>__በአካል ላይ ጉዳት__<br>• ለሰውነት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መንፈግ<br>• በሀይል መገፍተር<br>• መደብደብ ወይም መርገጥ<br>• በጥፊ መምታት፣ መንከስ፣ወይም መቆንጠጥ<br>• በሀይል ማወዛወዝ እስኪበልዙ ድረስ<br>• መምታት፣ማላጋት፣በቡጢ መምታት፣<br>• አሥሮ መደብደብ ወይም በቡጢ መምታት<br>• ምግብ፣መድሐኒት ወይም እንቅልፍ መንፈግ<br>• ማቁሰል፣አጥንት መሰበር፣ በውስጥ ሰውነት ላይ ጉዳት ማድረስ<br>• መሣሪያ መጠቀም ወይም ሌላ ዕቃዎችን እንደ መሣሪያ መጠቀም<br>• አካለ ጎደሎ ማድረግ<br>• መግደል<br><br>__ማስፈራራት__<br>• አስፈላጊ የሆኑ ሰነድዎችዎን መደበቅ ወይም ማጥፋት (ፓስፖርትዎን፣ የልጆችዎን ፓስፖርት፣መታወቂያ ካርድ፣ ግሪን ካርድ የመሳሰሉትን)<br>• የቤተሰብዎችዎን ፎትግራፍ ማጥፋት<br>• ከአገርዎ ያመጡትን እቃ/ሀብት ማጥፋት<br>• ድጋፍ የሚሰጠትን ሰው፣ ዘመድዎችዎን፣ጓደኝዎችዎን ማስፈራራት<br>• የቤተሰብ ሚስጥር አወጣለሁ ብሎ ማስፈራራት<br>• እራስ በራስን ማጥፋት እንደማስፈራሪያ መጠቀም<br>• አገርዎን፣ሥራዎን፣ፆታዎን ማንቋሸሽ<br>• ንብረትዎን ማጥፋት ወይም ማበላሸት<br>• ሀይለኝነትን/ጥንካሬን ማሳየት | የኢኮኖሚ ጉዳት<br>• የሥራ ፈቃድ ሳይኖርዎ ከሕግ ውጪ በሆነ መንገድ ሥራ እንዲሠሩ ማስገደድ<br>• ተደብቀው ከሆነ የሚሠሩት ለ ኢምግሬሽን እነግራለሁ እያሉ ማስፈራራት<br>• እንዳይማሩ ወይም የሥራ ስልጠና ትምህርት እንዳያገኙ መከልከል<br>• አገር ቤት የሚልኩትን ገንዘብ መውሰድ<br>• የቤተሰቡን ገቢ/ገንዘብ እነዳይነኩ ወይም እንዳያውቁ መከልከል<br><br>__ማግለል/ለብቻ መነጠል__<br>• ከቤተሰብና ከጓደኛ መነጠል<br>• እንግሊዘኛ እንዲማሩ አለመፍቀድ<br>• በራስዎ ቋንቋ እነዲናገሩ አለመፍቀድ<br>• ደብዳቤዎን ማንበብ ወይም ስልክ እንዲያወሩ አለመፍቀድ<br>• በቋንቋዎ የተጻፉ መፅሔቶችን እና ጋዜጦችን እንዳያገኙ ማስቀም፣ ያሎትንም ማጥፋት<br>• የእርስዎን ቋንቋ ከሚናገሩ፣ ከእርስዎ ማህበረሰው ከሆኑ፤ከእርሶ ባህል ወይም አገር ከመጣ ሰው ጋር እንዲገናኙ አለመፍቀድ<br>• ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ሁሉ ማጥፋት<br>• ዘመድዎችዎንና ጓደኞችዎን ማግለል<br><br>__ልጆችን መጠቀም__<br>• ልጆችዎን ከዚህ አገር ወደሌላ አገር እወስዳለሁ ብሎ ማስፈራራት<br>• ልጆችዎን ለኢሚግሬሽን ሪፖርት አደርጋለሁ እያሉ ማስፈራራት<br>• ለልጆችዎ ማሳደጊያ ወደ አገርዎ ለመላክ ያቀዱትን ገንዘብ መውሰድ<br>• እርስዎን ከዚሁ አገር አስወጣለሁ ልጆችዎን እዚህ አስቀራለሁ ብሎ ማስፈራራት<br>• እርዳታ ከፖሊስ ወይም ከፍርድቤት ከጠየቁ የዚሁ አገር ሕግ ልጆቹን ለአጥቂው እንዲያሳድግ እንደሚፍቀድ |

| | |
|---|---|
| • በእንግሊዝኛ የተጻፉ ወረቀቶችን ምን እነደሆኑ ሳያውቁ እንዲፈርሙ ማስገደድ (የፍርድ ቤት ወረቀት፣ የአይአርኤስ ሰነድ፤የ ኢምግሬሽን ወረቀት) | ይነግርዎታል |

## ኢሚግሬሽንና የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት እና ሕገ ወጥ የኬላ ማሻገር ጥቃት ለተጋለጡ ኢሚግራንቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የሚከላከልላቸው ልዩ ሕግ አለ።

ነገር ግን ጠበቃዎን ወይም አድቮኬቶችን ሳያማክሩ ኢሚግሬሽን አይሂዱ

የአሜሪካን መንግስት ቫዮለንስ አጌነስት ዊሜን አክት (ቫዋ) የሚባል ሕግ ተጨማሪ የሕግ መከላከያና በወደፊት ኑሩዎ ላይ የበለጠ ቁጥጥር እንዲያደርጉ የሚረዳዎ ሕግ ደንግጎዋል።

አሜሪካዊ ዜግነት ያለው ወይም ቋሚ ነዋሪነት ያለው ሰው ያገቡና ለተጠቁ ኢምግራንት ሴቶች ሕጋዊ ነዋሪነት ለማግኘት የሚስችላቸው ሁለት መንገድ ፈጥሮዋል።

አይ-360 - ሰልፍ ፔትሽኒንግ/ለራስ ማመልከት የነዋሪነት ማመልከቻ ባልዎ ለዩናይትድ ስቴትስ ዜግነት እና ኢምግሬሽን አገልግሎት (ዩኤስሲአይኤስ) የቀድሞው ኢምግሬሽን እና ናቹራላይዜሽን ሰርቪስ (አይኤን ኤስ) እንዲያስገባልዎ ከመጠበቅ ወይም የሱን እርዳታ ከመፈለግ ለእርሶ እና ለልጆችዎ እራስዎ ማመልከት ይችላሉ። ባልዎ በዚህ ሂደት ውስጥ ምንም ዓይነት ሚና አይጫወትም ለነዋሪነት እንዳመለከቱም ማወቅ የለበትም።

አይ-751 - ካንስሌሽን ኦፍ ሪሙቫል/የመውጣት ትዕዛዝ ስረዛ፦ ይህ የሚያገለግለው ከአገር እንዲወጡ የሚል ፍርድ ላይ ካሉ ነው ለካንስሌሽን ኦፍ ሪሙቫል ጉዳይዎ የተሟላ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ካገር እንዲወጡ ያዘዘውን ትቶ የነዋሪነት ፍቃድ ሊሰጥዎ ይችላል፡ ሆኖም ማመልከቻ ማስገባት የሚችሉት ካንስሌሽን ኦፍ ሪሙቫል/የመውጣት ትዕዛዝ ውሳኔ ከተሰጠ ነው እርግጠኛ ለመሆን የኢምግሬሽን ጠበቃ ያናግሩ።

ይህ ሕግ የተወሳሰበ ነው በቅድሚያ የመጠለያ ሠራተኛ፤ የኢሚግሪሽን ሠራተኛ ወይም የቤት ወስጥ ግጭት/ሁከት ድርግት፤ የኢምግሬሽን ድርጅት ሳያማክሩ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ዜግነት እና ኢምግሬሽን አገልግሎት (ዩኤስሲአይኤስ) አይሂዱ።

ለቫዋ ለማመልካተ በቂ ካልሆኑ አይዘኑ የነዋሪነት ፈቃድ ሊያገኙባቸው የሚያስችሎት ሌላ መንገድ ይኖራል። አነዱም ለምሳሌ ያህል አዲስ ቪዛ ነው። ይህ ኮንግረስ ወንጀል ለተፈጸመባቸው እንዲረዱ የፈጠለው ነው ፡

ሕገ ወጥ የኬላ ሽግግር

ሰዎችን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ኬላ ማሻገር /ማጓጓዝ ሌላው ዓይነት ጥቃት ነው። ሰዎችን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ኬላ ማሻገር በአለም አቀፍ ደረጃ የሰውን ልጆች መብት የሚጋፋ ነው። ስለዚህ ጉዳይ በበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን ተቋሞች ያነጋግሩ፡

- ዩናይትድ ኔሽንስ ኦፊስ ኦን ድራግስ ኤንድ ክራይም
- ዩ.ኤስ. ስቴት ዲፓርትመንት